# አሻፈረኝ በኢትዮሚድያ

**ከብርቱ ምሰሶ**

ለተመለከተው ሊያስገርም ይችላል። አስገራሚው ግን የብዕር ስሙ በዚያ የብዕር ስም የሚታወቀው ግለሰብ ሆኖ አለመገኘቱ ነው። ይህን የምለው ሰሞኑን የተፃፈ ፅሁፍ " የአዛኝ ቅቤ አንጓችነት ወይንስ አህያዉን ፈርተዉ ዳዉላዉን ?" በሚል ርዕስ ኢትዮሚድያ ላይ ቀርቦ ሳገኘው ገርሞኝ እና ደንቆኝ ነው። ፀሀፊው ናቸው ብዬ የምጠብቀው ግለሰብ ራሳቸውን ሆነው አለመገኘታቸው ዝቅጠትን የተላበሰ አካሄድ ነው ብዬ ለመደምደም ተገድጃለሁ።

ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ሀሳብ አለኝ ብሎ የሚያስብ ግለሰብ ወይንም አካል እና በተለይም የሀገሪቱን ህዝብ ልመራው እንዲሁም በህዝብ ፊት ልቆም ተዘጋጅቺያለሁ ለሚል፣ እኔ ካልመራሁት ሊሆን አይችልም ብሎ እመደምደም ደረጃ ላይ መድረስ ሊያስደንቀን ይችላል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በፖለቲካው ሂደት ላይ የራሱ የሆነ አመለካከት ሊኖረው እንደሚችል ማንም እንደማይዘነጋው ግልፅ ነው፤ነገር ግን አንድ የፖለቲካ መስመር ብቻ በማንኛውም ወገን ላይ በማስገደድ ለማስያዝ መሞከር ወይንም እኔ የያዝኩት የፖለቲካ አካሄድ ተኮነነብኝ፣ እና ተተቸብኝ "ያዙኝ ልቀቁኝ" ቢባል ሁኔታው "የመፃፍ እና የመናገር መብት ተከራካሪ ነኝ።" ከሚል ግለሰብ ወይንም አካል የሚታይ ከሆነ አካሄዱ አጠያያቂ ነው።

ቢንዳ(bogus) የብዕር ስም ተጠቅመው ሀሳባቸውን ከላይ በጠቀስኩት ርዕስ የፃፉት ግለሰብ የዘነጉት ነገር ቢኖር፤ ምንም ቢሆን ሊነቃነቅ እና ሊገፉ የማይችል የህዝብ አካልን ለመንቀፍ መሞከራቸውን ነው። ጭራሹኑ ከድጋፉ እንዲርቅና እንዲሸሽ በጣም ያለውን ክፍተት እያሰፉት እና አክ-እንትፍ እንዲላቸው(ለነገሩ "ቱፍ" ካለ ቆየ) እየሞከሩ ነው።

አሁን እስቲ ስዬ አብርሃ ተነቀፈ ወይንም ተተቸ ብሎ ለምቦጭን መዘርጋትን ምን አመጣው? ስዬ በራሱ ዘዴ እና ስልት የያዘው መንገድ ሊዋጥላቸው የማይችሉ ብዙ ወንድሞችና እህቶች ይኖራሉ። እነዚህ እህቶችና ወንድሞች የራሳቸውን አመለካከት በማንኛውም መንገድ ተደራጅተውም ይሁን በግላቸው አስተያየታቸውን መስጠታቸው ምኑ ላይ ነው ጥፋቱ? ለዚያውም በሀገሪቱ አንድነት እና ሁኔታ ላይ ትልቅ ደባ ፈፅሞ ሀገሪቱን እያጠፉት ካሉት "ወያኔዎች" ጋር በጥቅም ተጣልቶ ዘብ-ጥያ ከወረደ ግለሰብ!!! እና ዝም በሉ የሚባለው ለዚህ ነው?! ስንት ነፁሐን ኢትዮጵያውያኖች ናቸው በሲዬ ትዕዛዝ አማካኝነት ህይወታቸውን ያጡት?! አሁን ሲዬን መልሰን ስልጣን ላይ ካልሰቀልነው በኢትዮጵያ ውስጥ ሊመጣ የሚችለውን ለውጥ ልናይ አንደማንችል ተደርጎ መታየቱ ራሱ "ሳታመሀኝ ብላ..." ያስመስለዋል።

እስቲ አንድ ጥያቄ አለኝ። ሲዬ አብርሃ የአሁኑ ተቃዋሚ ሆኖ ሲገኝ ደጋፊ መሆን አለባችሁ ከሆነ ጉዳዩ፤ እንዴት ባለስልጣን እያለ ሊገድለን ሽጉጡን ይዞ ሲንጎራደድ "ተው" አላላችሁት? ያኔ አዎ አንዳንዶቻችሁ በአካል ትተዋወቁ ነበር። አብራችሁ ትበሉ ትጠጡ ነበር። አሁን ደግሞ ከመለስ ዜናዊ ጋር በአላቸው የግል ጥል ምክንያት ሲዬ ከወያኔ ካምፕ ቢወጣም ወያኔን በምኑም ሊጠላው እና ከልቡ ሊወጣም አይችልም። ሲዬ ሰለ ሰላማዊ ትግል ሊነግረኝ ከሞከረ ምን ያህል ቂል አድርጎ ቢያየኝ ነው ብዬ መጠርጠሬ እና አለማመኔ ምኑ ላይ ነው ክፋቱ? ፖለቲካ በግድ?! ወቸው ጉድ! ፖለቲከኞች እኮ ሊተቹ እና ህዝቡ እንዲሁም ማንኛውም ማንነታቸውን የሚያውቃቸው ግለሰብ ሊያናግራቸው፣ ሊተችባቸው፣ ላይ አንስቶ ታች ሊያፈርጣቸው እንደሚችል ማወቅ አለባቸው። በዚህም ምክንያት ፓልቶክ ሩሞች ውስጥ ገብቶ

ሃሳቡን የሚገልጸውን ህብረተሰብ ምስጋና ይገባዋል። ሀሳቡን በሀገሩ ጉዳይ ላይ መግለፅ የሚችል ትውልድ ማፈራቱ በራሱ አጥጋቢ ነው። ይቀጥሉበት!!!

ግንቦት 7 አቅም ኖሮት የከረንት አፌየርስ አድሚኖችን በቁጥጥሩ ስር ካዋለ፤ ምን ማድረግ ይቻላል? የግንቦት 7 ሰዎች ስር የሰደደ እንቅስቃሴ አድርገዋል ማለት ነው። የሲዬም ሰዎች ስር የሰደደ እንቅስቃሴ አድርገው የከረንት አፌየርስ አድሚኖችን ለመያዝ የሚችሉ ከሆነ ከመሞከር ወደኋላ አለማለት ወንድማዊ ምክሬ ነው፤ ከተሳካ ማለቴ ነው። የከረንት አፌየርስ አድሚኖች ውስጥ ሁሉም የሲዬ አብርሃ ተቃዋሚ ላለመሆናቸው ከላይ ያሰፈርኩት ርዕስ ፀሓፊ ራሳቸው ባሰፈሯቸው ሐረጋት እና ዐረፍተ-ነገሮች አስረግጠውልን እንዳለፉ ለማሳየት እሞክራለሁ። አንቀፁ እንዲህ ይላል :- "ይሁን እንጂ ይህንን የተናገሩትን ሀቅ እርሳቸዉ የሚመሩትን G7 የሚደግፉና በድርጅቱ ዉስጥ አባል ሆነዉ የሚንቀሳቀሱ ምንም እንኳን ዛሬ በትግል ስልት ብንለያይ ለአንድ ዓላማ የምንታገል የትግል አጋሮቻችን ናቸዉ ብለን እምነት የምንጥልባቸዉ ዎንድሞቻችንና እህቶቻችን ባንድ በኩል ወይዘሪት ብርቱካንን የደገፉ በመምሰል የአዞ እንባ ሲያነቡ በሌላ በኩል ግን እርሳቸዉ የመሰረቱትን ድርጅት ለማፍረስ በካረንት አፌይርስ (Ethiopian Current Affairs) አድሚኖች ጠቅላላ ስብሰባ ዉሳኔ ተላልፎ በተቀናጀ መልኩ ዘመቻ በማካሄድ ላይ መሆናቸው የአዛኝ ቅቤ አንጓች መሆን ብቻ ሳይሆን የጸረ ወያኔው የትግል መስመር ወዴት እየተገፉ ነው የሚል ጥያቄ እየጫረብን ይገኛል።" ። እንዲህ ከሆነ ዘንዳ እስዎም ከከረንት አፌየርስ አድሚኖች አንዱ ነዎት ማለት ነው። እስዎ ሊጭኑባቸው ያሰቡት አካሄድ አላስኬድ ካለ ሁሉንም በገፍ መነቀፉ አግባብ ያለው አይደለም።

በኢትዮጵያ ያለው ትግል ችግሩ ያለው የተቋቋሙት ቡድኖች ላይ ሳይሆን እናቀሳቅሰዋለን የሚሉት ግለሰቦች ላይ ነው። ለዚህም ነው አሁን ሲዬ እመራዋለሁ እያለ ታች ላይ የሚዋኝበት "አንድነት ፓርቲ" ላይ ትልቅ ችግር የመጣው። አንድነት ፓርቲ ያለሲዬ ሊንቀሳቀስ እንደማይችል ተደርጎ የሚነዛው ቅስቀሳ በራሱ ተቀባይነት ቢያጣ ምንም አጠያያቂ አይሆንም። ምክንያቱም የድርጅቱ መሪ እና መስራች አባል በአሁኑ ሰዓት እስር ቤት እየማቀቀች ትገኛለች። ስለዚህ ለስዬም ሆነ ለነጋሶ የነቀፌታ አስተያየት ቢደርሳቸው "አሜን" ብሎ የመቀበል ግዴታ አለባቸው። ስዬም ሆነ ነጋሶ አሁን ኢትዮጵያን በሀይል እየገዛ ባለው ቡድን ውስጥ ውስኪ ሲራጩ እና በንፁሐን ደም ላይ ሲያሾፉ የነበሩ የቀድሞ ታላላቅ ባለስልጣናት የነበሩ ናቸው። ምነው ያኔ ኢትዮጵያውያን መበደላቸውን፣መሰቃየታቸውንና መገደላቸውን ዘነጉት? የዘነጉትማ እራሳቸው በዳዮች፣አሰቃዮች፣ እንዲሁም የግድያ መስኩን አዘጋጆች ሆነው መንበረ-ስልጣኑ ላይ ደልቷቸው ስለተቀመጡ ነው። ሌላ ምን ሊባል ይቻላል?! ህሊናማ ያለው የሚመራውን ሃይል እንዳትገድሉ፣እንዳትበድሉ እና እንዳታሰቃዩ ብሎ ትዕዛዙን ያስተላልፍ ነበር። ነገር ግን ስዬ የመከላከያ ሚንስትር በነበረበት ወቅት ፡ እንዲሁም ነጋሶ ጊዳዳ ፕሬዝዳንት በሆነበት ጊዜ ደሀው ቢሞት፣ቢበደል እና ቢሰቃይ ምንም አይደል?! ይሄማ ህሊና ላለው ነውር ነው!

ለማጠቃለያ ያህል እኔ በድጋፍ ደረጃ የማገለግለው የ"አንድነት" ፓርቲ በእነ ሲዬ የሚመራውን አይደለም። በእኛም ውስጥ አንዳንዶች እንደሚያደገድጉ አውቃለሁ። ግን የትም እንደማይደርሱ ሁላችንም ስለምናውቅ ያን ያህል ቦታ አንሰጣቸውም። በተጠንቀቅ ቆመን እየተከታተልናቸው ነው። ስለዚህ በአጠቃላይ የድርጅቱ መሪ "ብርቱካን ሚደቅሳ" እንደምትባል ለሰሞኑ የሲዬ እና ነጋሶ ደጋፊዎች ልናሳውቃችሁ እንወዳለን።